


# +++ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ +++

# የዕለት እንጀራ

መጋቢት ፲፫ **ማቴዎስ ፳፬:፩-፴፮** ፳፻፩




የዐቢይ ጾም እያንዳንዱ ሳምንት (እሁድ) ከጌታችንና አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርትና ስራ ጋር በተያያዘ ስም ተስጥቶት ተከፍሏል:: ይህ ሳምንት ደብረ ዘይት ይባላል:: ደብረ ዘይት ጌታችንና አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአቱን በተለመለከተ ያስተማረበት ተራራ ነው::

አሁንስ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ በፍጹም ልባችሁ፥ በጾምም፥ በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ። ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ። ኢዮ ፪:፲፪-

ኢየሱስም ከመቅደስ ወጥቶ ሄደ፥ ደቀ መዛሙርቱም የመቅደሱን ግንቦች ሊያሳዩት ቀረቡ። እርሱ ግን መልሶ:- ይህን ሁሉ ታያላችሁን? እውነት እላችኋለሁ፥ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም አላቸው።

እርሱም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው። ንገረን፥ ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው? አሉት።

ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው:- **ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ።**

ብዙዎች -እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ።

ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ፥ አትደንግጡ፤ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው።

ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና፥ ራብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል፤ እነዚህም ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው።

በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል ይገድሉአችሁማል፥ ስለ ስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ።

በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ እርስ በርሳቸውም አሳልፈው ይሰጣጣሉ እርስ በርሳቸውም ይጣላሉ፤ ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፤ ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች።

**እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።**

ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል።

እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን **የጥፋትን ርኵሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ፥ አንባቢው ያስተውል፥**

አምላካችሁም እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ፥ ቍጣው የዘገየ፥ ምሕረቱም የበዛ፥ ለክፋትም የተጸጸተ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ። ኢዮ ፪: ፲፫

## የዐቢይ ጾም ሳምንት:

## ደብረ ዘይት

| ምስባክ | ትርጉም |
|---|---|
| እግዚአብሔርሰ ገሀደ ይመጽእ<br>ወአምላክነሂ ኢያረምም<br>እሳት ይነድድ ቅድሜሁ<br>መዝ ፵፱፡፪-፫ | እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል።<br>አምላካችን ይመጣል ዝምም አይልም<br>እሳት በፊቱ ይቃጠላል |